ት-ሣ-ግ§ን
ፕ6/ሪ/10

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር 3·5·0/34/10
Ref. No.
ቀን 11 ጥቅምት 2010
Date

በአባሪ ለተዘረዘሩት በሙሉ

<u>በያሉበት፣</u>

ጉዳዩ፡- <u>ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሶ ማስቀረትን ይመለከታል፡፡</u>

ናሽናል አጠቃላይ ሆስፒታል በትርፍ ጊዜያቸው ከሆስፒታላቸው ጋር ፕሮግራም አድርገው የሚሠሩ እስፔሻሊስት ሀኪሞችና ባለሙያዎች ከሚያገኙት ገቢ ላይ 30% ቅድመ ግብር ቀንሰው የሚከፍሉ መሆኑን፣ ነገር ግን ሌሎች ሆስፒታሎች 2% እንደሚቀነስና ይህ ወጥ ያልሆነ አሠራር በድርጅቱ ላይ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት እያስከተለ መሆኑን በመጥቀስ ወጥ የሆነ መመሪያ እስኪተላለፍ 2% ከሚያገኙት ክፍያ ላይ ቀንሰው በማስቀረት ማስተናገድ እንዲችሉ በ12/01/2010 ዓ/ም በቁጥር NGH/10/2010 በተፃፈ ደብዳቤ ጠይቀዋል፡፡

ጉዳዩን አስመልክቶ ከሐምሌ 1 ቀን 2008 ዓ/ም ጀምሮ ተግባራዊ በሆነው ከፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 እና አዋጁን ለማስፈጸም ስለፌደራል የገቢ ግብር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 410/2009 መሠረት ተፈጻሚ የሚደረግ በመሆኑ ለቀረበው ጥያቄ ከዚህ እንደሚከተለው ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

የፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 7 "ተቀጣሪ" ማለት ራሱን ችሎ የሚሠራን የሥራ ተቋራጭ ሳይጨምር በሌላ ሰው መሪነትና ቁጥጥር ሥር ሆኖ አገልግሎት ለመስጠት በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት የተቀጠረ ግለሰብ ሲሆን የድርጅት ዳይሬክተርን ወይም በድርጅቱ አመራር ውስጥ ኃላፊነት የተሰጠውን ሌላ ሰው እንዲሁም ተሿሚንና የሕዝብ ተመራጭን ጨምሮ የመንግሥት ሥራ ኃላፊን ያጠቃልላል በሚል ትደነግጋል፡፡ በመሆኑም

1. ባለሙያዎቹ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት አገልግሎት ለመስጠት የተቀጠሩ ከሆነ በአዋጁ አንቀጽ 88 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ቀጣሪው ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለተቀጣሪው በሚከፈልበት ጊዜ ተቀጣሪው ከአንድ በላይ የሆነ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ እንዳለው ያወቀና ሌላው ቀጣሪ ወይም ሌሎቹ ቀጣሪዎች በጠቅላላው የተቀጣሪው ገቢ ላይ ተመስርተው የገቢ ግብሩን ቀንሰው እንደማያስቀሩ ያወቀ እንደሆነ ቀጣሪው የተቀጣሪውን ገቢ በማጠቃለል ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ግብር ቀንሶ ማስቀረት ግዴታ እንዳለበት፣
2. የሥራው ዓይነት ከቅጥር ጋር ግንኙነት የሌለው አገልግሎት ከሆነ ከሀገር ውስጥ ከሚፈጸሙ ክፍያዎች ላይ ግብር ቀንሶ ስለማስቀረት በአዋጁ አንቀጽ 92 በተቀመጠው ድንጋጌ እና

ለዘመናዊና ፍትሐዊ የታክስ አሰባሰብ ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን!!

አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 410/2009 አንቀጽ 63 መሠረት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የንግድ ስራ ፈቃድ ሲያቀርብ ከክፍያው ላይ 2% ቅድመ ግብር ተቀናሽ የሚደረግ ሲሆን አገልግሎት አቅራቢው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና ንግድ ስራ ፈቃድ ማቅረብ ያልቻለ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 92 ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ በተገለጸው መሰረት 30% ከጠቅላላው ክፍያ ላይ ተቀናሽ መደረግ ያለበት መሆኑን፣

በግልጽ ተደንግጓል፡፡

በመሆኑም ከላይ በተራ ቁጥር 1 እና 2 በተገለጸው መሠረት ባለሙያዎቹ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት አገልግሎት ለመስጠት የተቀጠሩ ከሆነ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ግብር መክፈል ያለበት መሆኑን፣ የሥራው ዓይነት ከቅጥር ጋር ግንኙነት የሌለው አገልግሎት ከሆነ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የንግድ ስራ ፈቃድ ሲያቀርብ ከክፍያው ላይ 2% ቅድመ ግብር ተቀናሽ የሚደረግ ሲሆን አገልግሎት አቅራቢው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና ንግድ ስራ ፈቃድ ማቅረብ ያልቻለ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 92 ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ በተገለጸው መሰረት 30% ከጠቅላላው ክፍያ ላይ ተቀናሽ ተደርጎ ለገቢ ሰብሳቢ አካላት ገቢ መደረግ እንዳለበት ያሳያል፡፡

ይሁንና ቀደም ሲል ከባለስልጣን መ/ቤታችን በቁጥር 3.0/487 በ27/07/2006 ዓ/ም የሌላ መ/ቤት ሠራተኞች የሆኑ ሰዎች ራሳቸውን ችለው ከተቀጠሩበት መ/ቤት ውጭ ለሰሩት ክፍያ ሲፈጸም ግብር ቀንሰው የማስቀረት ኃላፊነት ያለባቸው አካላት ክፍያ ሲፈፅሙ ያለባቸው ግዴታ አገልግሎት አቅራቢው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ካለው 2% ከሌለው 30% ቀንሰው ለታክስ ገቢ ሰብሳቢ አካላት ገቢ ሲያደርጉ መረጃውን ጭምር መስጠት እንደሚገባቸው ተገልጾ የተላለፈው ሴርኩላር የፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 እና ደንብ ቁጥር 410/2009 ድንጋጌ መሠረት ከሐምሌ 1 ቀን 2008 ጀምሮ በተገኘ ገቢ ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

ስለዚህ የገቢ ሰብሳቢ ተቋሟት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሰው የማስቀረት ኃላፊነት በህግ የተጣለባቸው አካላት ይህንን አውቀው እንዲፈጽሙ በማናቸውም የመገናኛ ዘዴዎች በመጠቀም እንዲገለጽላቸው ከማድረግ በተጨማሪ ከላይ በተጠቀሰው አግባብ ተፈፃሚ እንዲሆን የሚመለከታቸው ሀላፊዎችና ሰራተኞች እንዲያውቁትና በዚሁ መሠረት ስለመፈጸሙ ተገቢው ክትትልና ድጋፍ እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር//

አካያንቺ አባተ
የግብር አወሳሰንና አሰባሰብ አሰራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክ

ግልባጭ፡-

- ለፌደራል ሀገር ውስጥ ታክስ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ስራዎች ዘርፍ
- ለአዲስ አበባ ሀገር ውስጥ ታክስ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ስራዎች ዘርፍ
- ለፌደራል አገር ውስጥ ታክስ ጉዳይ ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ አዲት አሠራርና ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለክልሎች ድጋፍና ትብብር ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለኢንቨስትጌሽን አዲት ዳይሬክቶሬት
- ለደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለትምህርትና ኮሚኒኬሽን ዳይሬክቶሬት

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

- ለናሽናል አጠቃላይ ሆስፒታል (0116-622832)

አዲስ አበባ